የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) እውነታዎች

Tuberculosis (TB) Facts (Amharic)

ለቲቢ መጋለጥ

ቲቢ ምንድን ነው?

“ቲቢ” ሳንባ ነቀርሳ ተብሎ የሚታወቀው በሽታ በአጭሩ ሲጠራ ነው። ቲቢ በአየር ውስጥ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋል። አንድ በሳንባ ወይም በጉሮሮ **ቲቢ በሽታ** የታመመ ሰው ሲያስለው፣ ሲናገር፣ ሲስቅ፣ ሲዘፍን፣ ወይም ሲያስነጥሰው የቲቢ ጀርሞች በአየር ውስጥ ይተላለፋሉ። የ**ቲቢ በሽታ** ካለበት ሰው አጠገብ የሚገኝ ማንኛው ሰው የቲቢ ጀርሞችን ወደ ሳንባው ውስጥ ሊተነፍስ ይችላል።

የቲቢ ጀርሞች ሳያሳምሙዎት ሰውነትዎ ውስጥ ሊቆዩ ይችላሉ። ይህ **ሌተንት ቲቢ ኢንፌክሽን** ይባላል። ይህም ሰውነትዎ ውስጥ የማይራቡ(የተኙ) የቲቢ ጀርሞች ብቻ አሉ ማለት ነው። የማይራቡት ጀርሞች ወደ ሌላ ሰው ሊተላለፉ አይችሉም። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ጀርሞች ከነቁ ወይም ሰውነትዎ ውስጥ መራባት ጀምረው ከተባዙ፣ በ**ቲቢ በሽታ** ይታመማሉ።

የቲቢ ጀርሞች ሲራቡ (ሰውነትዎ ውስጥ ሲባዙ)፣ **ቲቢ በሽታ** ይባላል። ጀርሞቹ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠቁት ሳንባን ነው። ሌሎች የሰውነት ክፍሎችንም ሊያጠቁ ይችላሉ፣ እንደ ኩላሊት፣ አንጎል፣ ወይም አከርካሪ የመሰሉትን። የ**ቲቢ በሽታ** እንዲታመሙ ያደርጋል። የ**ቲቢ በሽታ** የያዛቸው ሰዎች አብረዋቸው ለሚኖሩት ሰዎች ጀርሞቹን ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

ለቲቢ የተጋለጥኩት እንዴት ነበር?

የሳንባ ወይም የጉሮሮ **ቲቢ በሽታ** ከያዘው ሰው አጠገብ ቆይተው ከነበረ ለቲቢ ተጋልጠው ሊሆን ይችላል። በበሽታው ሊለከፉ የሚችሉት አንድ ሰው ወደ አየር ካሳለው በኋላ ጀርሞቹን ወደ ውስጥ ሰውነትዎ ሲተነፍሱ ብቻ ነው። ከአንድ ሰው ልብስ፣ የመጠጫ ብርጭቆ፣ የምግብ ዕቃዎች፣ እጅ በመጨበጥ፣ ወይም በቲቢ የታመሙት ሰው ከነበሩበት ሌላ ሥፍራ ቲቢ ሊይዝዎት አይችልም።

በቲቢ ጀርሞች ተለክፌ እንደሆን የማውቀው እንዴት ነው?

የ**ቲቢ በሽታ** ከያዘው ሰው አጠገብ ቆይተው ከነበረ፣ ለምርመራ ወደ ሐኪምዎ ወይም ወደ አካባቢዎ ጤና ጥበቃ ክፍል መሄድ ያስፈልግዎታል።

የ**ቲቢ ኢንፌክሽን** (በቲቢ መለከፍን) ለይቶ ለማወቅ ሊረዱ የሚችሉ ሁለት ዓይነት ምርመራዎች አሉ፤ የቲቢ ቆዳ ምርመራ ወይም የቲቢ ደም ምርመራ ናቸው። የቆዳ ምርመራ ብዙ ጊዜ ይደረጋል። ጥቂት መመርመሪያ ነገር፣ ቱበርክሊን የሚባለው፣ በትንሽ መርፌ ቆዳ ውስጥ ተወግቶ ይጨመራል። ሰውነትዎ ምን ዓይነት ምልክት እንደሰጠ ምርመራ ወደሚያደርጉልዎት የጤና ጥበቃ ሠራተኛ ከ 2 እስከ 3 ቀናት ውስጥ ተመልሰው ይሄዳሉ። ለአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የቲቢ ደም ምርመራ የ**ቲቢ እንፌክሽንን** ለመመርመር ያገለግላል። ይህ የደም ምርመራ የአንድ ሰው የተፈጥሮ በሽታ መከላከያ ዘዴ ለቲቢ ጀርሞች ምን ዓይነት ምልክት እንደሚያሳይ ይለካል።

አንድ ሰው የ**ቲቢ በሽታ** እዳለበት ለይቶ ለማወቅ፣ እንደ ራጅ(ኤክስሬይ) እና የአክታ ናሙና (ከውስጥ ከሳንባ በሳል የሚወጣ ወፍራም ትፋት) የመሰሉት ሌሎች ምርመራዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ።



http://www.cdc.gov/tb

CS232274_B